
# መድሎተ ጽድቅ

## የእውነት ሚዛን

ቅጽ ፲



ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

CamScanner

# ምዕራፍ ሰባት

## ክርስትና እና ቁሳዊ ብልጽግና

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ጉዳይ፣ የአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግና የዚያ አገር ሕዝብ የሚከተለው ሃይማኖት ትክክለኛ የመሆኑ ውጤት ነው ወይስ አይደለም? የሃይማኖት ትክክለኛነት መለኪያውና መገለጫውስ ምድራዊ ሥልጣኔና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ነው ወይስ አይደለም? የሚሉ መሠረታዊ ጉዳዮችን ነው። ከዚህም "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ" የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ጸጋ አብ በቀለ፣ የአውሮፓ ዕድገትና ሥልጣኔ የእነ ሉተር የተሐድሶ ፕሮቴስታንት ውጤት ነው ብሎ፣ እና የደቡብ ኮሪያን የኢኮኖሚ ዕድገት ተሐድሶ ፕሮቴስታንት የመሆኗ ውጤት ነው ብሎ በድፍረት ደግሞ ደጋግሞ የጻፈ በመሆኑ፣ ይህ የጸሐፊው ሐሳብ ምን ያህል ተጨባጭነት ያለው ነገር ነው? የሚለውን እንመለከታለን።

እንደዚሁም ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ኋላ የቀረችውና በኢኮኖሚ ድሀ የሆነችው እንደ እነ ደቡብ ኮሪያ ተሐድሶ ፕሮቴስታንትን ባለመቀበሏ ነው የሚል ሐሳብ በመጽሐፉ በአጽንኦት ስለሚያራምድ፣ ለኢትዮጵያ "ኋላ ቀርነት" የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ተጠያቂ አድርጎ ስለሚወነጅል፣ እና በዓለም የሆኑና እየሆኑ ያሉ መልካም ነገሮችን ሁሉ የተሐድሶ ፕሮቴስታንት ውጤቶች አድርጎ ስለ ጻፈ እነዚህን ጉዳዮችም እንመለከታቸዋለን።

እንደ ተለመደው፣ መጀመሪያ ላይ ከተሐድሶ ፕሮቴስታንቱ ጸሐፊ መጽሐፍ ላይ ይህን የተመለከቱ ሐሳቦቹን እንጠቅሳለን።

- "በታሪክ የተረጋገጠው ሁለንተናዊ የአውሮፓ የለውጥና የዕድገት ምክንያቶች አንዱ የ16ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደሆነ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ። ይህም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ለውጥ ወሳኝ መሆኑን ያመለክታል። በአገራችን በተቃራኒው በተለይ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ "ተሐድሶ" የሚለው ቃል በአሉታዊነት መፈረጁ ለለውጥ ያለንን ጥላቻና ጫፍ የነካ ፍርሃት ተጠቂ

እንደሆንን ያመለክታል። ይህም በታሪክ ፊተኞች የነበርነውን የኋለኞች ሁሉ ኋላ አድርጎናል።" (ገጽ 35)

- "ወደ አገራችን ስንመጣ "ክርስትናችን" ሃይማኖተኞች አደረገን እንጂ ሕይወታችንን አልለወጠውም። ክርስትናችን አሉታዊ የረሃብና የእርስ በርስ የጦርነት ታሪካችንን፣ ለዘመናት ሲዋኸቅ የኖረውን ፖለቲካችንን፣ ዝንተ ዓለም ታማሚ ሆኖ የዘለቀ ኢኮኖሚያችንን፣ ለእርስ በርሳችን ያለንን የተንሻፈፈ አመለካከቶቻችንን አልሞረደም። . . ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ እንደ አገራዊ ባህል የሚወሰድ "ክርስትናችን" የዕድሜውን ያህል ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ እንደሚገባው አልጠቀመንም። ወደ ቃሉ ክርስትና ለመመለስ ካልፈቀድን ከእንግዲህም አይጠቅመንም። ክርስትና በኢትዮጵያ ያረጀ ቢሆንም አላደገም። ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ብቻ ክርስትናቸውን መሥርተው ተለውጠው ዓለምን ሲለውጡ የእኛ "ክርስትና" በአዋልድ፣ በገድላት፣ በድርሳናትና በኦሪታዊ መልኩ በዓለም አቀፋዊ ደረጃ አነጋጋሪ መሆኑ ጥያቄውን በውስጣችን ማጫር ሲገባው መጽሐፍ ቅዱስ በማይደግፈን ልዩ መሆን የሃይማኖት ትምክህተኞች ያደረገን ይመስላል።" (ገጽ 36)
- "የኋላ ቀርነታችን፣ የድህነታችን፣ የረሃብተኛነታችን፣ የስደተኛነታችን፣ የመንደርተኛነታችን መሠረትና ምንጩ በክርስትና ስም ድግምት አስማትና ጥንቆላ በማስፋፋታችን ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።" (ገጽ 41)
- "ያልታደሰውና በብዙ አስተምህሮዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ፊት ለፊት የሚላተመው አገር በቀል ክርስትናችን የዚህች ታላቅ ጥንታዊት አገር ውድቀት አንዱ ምክንያት ነው። . . . ቤተ ክርስቲያናችን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ታድሳ የሁለንተናዊ ተሐድሶ ፋና ወጊ ካልሆነች እንቅፋት መሆኗ ይቀጥላል።" (ገጽ 42)
- "በአገራችን ክርስቶስ ያልገነነበት አፋዊ ክርስትና መንሰራፋት ብቻ ሳይሆን የለውጥ ጠላቶች አድርጎናል። ዓለም ሁሉ በሁለንተናዊ የለውጥ ባሕር ሲዋኝ እኛ በነገር ሁሉ ከኋላ ቀርተን ዛሬም እንደ ቀዳሚዎቹ መፎከራችን ያሳዝናል።" (ገጽ 86)
- "በአጠቃላይ ተሐድሶ ለሳይንስ ግኝቶችና ምርምሮች የአዲስ ዘመን በር ከፍቶላቸዋል ቢባል የተጋነነ አይደለም። . . . ጆቢ ማርከት የተባለ ምሁር፡- እ. ኤ. አ በ2009 የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በሳይንስና በኢንዱስትሪው አብዮት ወቅትና በኋላ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንደ ተጫወተ ለሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ

*ባቀረበው ጥናቱ አመልክቷል። . . .* ጆቢ. ማርከት ለጥናቱ የተጠቀመባቸውን ምንጮች ሲገልጽ ማርቶን እ. ኤ. አ. በ1938 *"የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በእንግሊዝና በጀርመን የዘመናዊ ሳይንስ ማበብ ምክንያት ነው"* ያሉትን፣ ሕሊ የተባሉ ምሁር እ. ኤ. አ. በ1961 *"የፕሮቴስታንትን የማድረግ ምስጢር ሲገልጹ <u>በሰው ነጻነትና ለእግዚአብሔር ተጠያቂ በመሆኑ ላይ</u> ማተኮራቸውና ለአዲስ አስተሳሰብ ያላቸው የተከፈተ ልብ ነው"* ያሉትንና በተለይ በጀርመን ላይ ያደረገው ሰፊ ጥናት ወደዚህ ውጤት እንዳደረሰው ገልጾአል።" (ገጽ 258-9)

- "እ.ኤ.አ. በ2000 የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ በአገሩ ለኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ዞሀ ቺአ "የአሜሪካን ኢኮኖሚ ስኬት ምስጢር" ጥናት እንዲያደርግ የቤት ሥራ ሰጠ። በጊዜው ምሁሩ አማኝ አልነበረም። ምሁሩም "እግዚአብሔር የቦርዴ ሊቀመንበር ነው" የሚል አነጋጋሪ ጽሑፍ አቀረበ። ከዚያም "ቤተ ክርስቲያን ያለችበት የገበያ ኢኮኖሚ እና ቤተ ክርስቲያን አልባ የገበያ ኢኮኖሚ" በሚል ርእስ የመጨረሻ ጽሑፍ ይፋ አደረገ። በጥናቱም የአሜሪካ የኢኮኖሚ ምጥቀት ምስጢር በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ላይ በመቆማቸው፣ ከሙስና የፀዱ በመሆናቸው፣ ለእርስ በርሳቸው ያላቸው ቤተሰባዊ ፍቅርና በወንጌል ሥነ ምግባር በታነጹ ክርስቲያን ባለ ራእይ አባቶች በመመራታቸው መሆኑን በዝርዝር አመለከተ። ዶክተር ዞሀ ቺአ ለመንግሥት ጥናቱን ይፋ ካደረገ በኋላ እ. ኤ. አ. 2002 በገሃድ ክርስቶስ ኢየሱስን ተቀብሎ ተጠመቀ።" (ገጽ 278)
- "የምዕራባውያን ዕድገት ምስጢሩ ክርስትና ነው። . . . የእኛ የተገላቢጦሽ ነው። በክርስትና ከዓለም ሕዝብ በኩር እንደሆንን አፋችንን ሞልተን ብንናገርም ዓለም የሚያውቀን በረሃብ፣ በድርቅ፣ በስደት፣ በእርስ በርስ ጦርነትና በኋላ ቀሪነታችን ነው። ምዕራባውያንን የጠቀመው ክርስትና ለእኛ ለምን አልጠቀመንም? . . . ወንጌልን ከእነርሱ በፊት የተቀበልን ቢሆንም እነርሱን ረጂ ያደረገው ወንጌል እኛን ከተረጂነት ለምን አላወጣንም? የሚል ጥያቄ አለብን።" (ገጽ 280-

## 7.1 አጭር ምልከታዎች

ጉዳዮቹን ከመሠረታቸው ጀምሮ በቀጣዮቹ የዚህ ምዕራፍ ክፍሎች አንድ በአንድ የምንፈትሻቸው ቢሆንም፣ ከዚያ በፊት ግን ዝም ብሎ ለማለፍ የማያስችሉ ፈጠራዎችና ውሸቶች የሞሉበት ስለሆነ፣ በተጠቀሱት ሐሳቦች ውስጥ ካሉት ብዙ አሳዛኝ ነገሮች ውስጥ ጥቂት ነገሮችን አንሥተን እንለፍ።

1) ዋና ዓላማዬ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘውን መንገድ መስበክ ነው ብሎ የሚያምን የአንድ ግለሰብም ይሁን ቡድን የመጀመሪያ ተግባሩ

ሊሆን የሚገባው፣ ያ ስብከት ምን ያህል ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር አቅርቧል ወይስ አላቀረበም? የሚል ሊሆን ይገባል እንጂ ምን ያህል ቁሳዊ ብልጽግናና የኢኮኖሚ ለውጥ አምጥቷል? የሚል ሊሆን እንዴት ይችላል? ይህማ የፖለቲካ ፕሮግራሞችና የመንግሥታት መደበኛ ተግባር ነው። ተሐድሶ ፕሮቴስታንት ያደረገው ነገር ቢኖር ክርስትናን ለቁሳዊ ፍጆታና እርካታ አገልጋይ ወደ ማድረግ ምድራዊ አስተሳሰብ ማውረድ ነው። ይህን የተሐድሶን መሠረታዊ ባሕርይ የተረዱ ብዙ ምዕራባውያን ሰዎችም ጉዳዩ ቁሳዊ ምቾትና ድሎት ከሆነ፣ ይህን ለማሟላትማ ከክርስትና ይልቅ የተሻሉ ሌሎች አማራጮችንስ ለምን አንሞክርም? ወደሚል መንገድ መራቸው። በሂደትም ክርስትናን የይስሙላና የቀልድ አደረጉት፣ በመጨረሻም ከነጭራሹ ጠሉት። በምዕራቡ ዓለም በገሃድ የሚታየውን ሥር የሰደደ **ክርስትና ጠልነት** በዘመናት ሂደት ያመጣው በተሐድሶ ፕሮቴስታንቶች የተሰበከው ይህን መሰሉ የተሳሳተ "ክርስትና" ነው። የተሰበከላቸው ክርስትና ልክ እንደ ዔሳው መልካም የሆነ የምስር ወጥና እንጀራ ስለሚገኝበት ሁኔታ በመሆኑ ነው። የእነርሱ ልጆች የሆኑት በመልክ እኛን በመንፈስ ግን ወላጆቻቸውን የሚመስሉት የአገራችን ተሐድሶዎችም ያንኑ ሐሳብ እንደ አዲስ እያስተጋቡልን ይገኛሉ።

2) በዚያውም ላይ ለአውሮፓ ሁለንተናዊ ለውጥና ዕድገት አንዱ ምክንያት ተሐድሶ ፕሮቴስታንት ነው ብሎ ደጋግሞ ጽፏል። ይህን ጉዳይ በሳይንሳዊ መንገድ በብዙ ምሁራን በጥልቀት የተጠኑ የተለያዩ ጥናቶችን መሠረት አድርገን ከታች በቦታው ላይ እንመለከተዋለን። ይሁን እንጂ ብዙም ሳይንሳዊ መሠረት የሌለውን ተሐድሶ ፕሮቴስታንት ለአውሮፓ የኢኮኖሚ ዕድገት ታላቅ ሚና ተጫውቷል የሚለውን ሐሳብ ደግሞ ደጋግሞ ከማስተጋባት ባሻገር ተሐድሶ ፕሮቴስታንት በእነዚሁ አገሮች ውስጥ ለክርስትና መዳከምና መጥፋት ታላቅ አሉታዊ ሚና መጫወቱንስ ለምን አይናገርም? ሴኪዩላሪዝምን ከባሕርዩ ወልዶ ያስገኘ መሆኑንስ ለምን አይነግረንም? ተሐድሶ በባሕርዩ ክርስትናን የሚያጠፋ በሽታ መሆኑንና ይህም በተግባር የተገለጠና የተረጋገጠ ስለ መሆኑስ ለምን ትንሽ እንኳ ፍንጭ አይሰጥም?

3) "<u>ክርስትናችን</u>" የዕድሜውን ያህል <u>ለምድሩም ሆነ ለሰማዩ እንደሚገባው</u> <u>አልጠቀመንም</u>" ይላል። ክርስትናችን ለሰማዩ ሕይወት እንደሚገባው ያልጠቀመን መሆኑን በምን አረጋገጠ? በምንስ አወቀ? ይህ የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ፍርድ አውቃለሁ የማለት የመጨረሻ ግብዝነት አይደለምን?

አንድ ሃይማኖት ወይም አስተሳሰብ በዚህ ምድር ላይ ለምቾትና ለድሎት አለመቀመም ማለት ለሰማዩም እንደማይጠቅም ማረጋገጫ ነውን?

4) በዚህ ዓለም ላይ ረጂና ተረጂ፣ ሀብታምና ድሀ መሆን የምናምነው እምነትና የተቀበልነው ወንጌል ትክክል ስለመሆን አለመሆኑ ማረጋገጫ ወይም መለኪያ አይደለም። ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርቱ ላይ ስለ ሁለት ሰዎች አስተምሯል። እነዚህም ባለጸጋው እና ድሀው አልዓዛር ናቸው። ስለ ባለጸጋው ሲናገር "ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፣ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር" ይላል። ስለ ድሀው ደግሞ "አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፣ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።"

ፍጻሜያቸውስ እንዴት ሆነ ይሆን? ጌታችን በማይታበል አምላካዊ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ብሎ ነግሮናል፡-

> ድሀውም ሞተ፣ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፣ አብርሃም አባት ሆይ፣ ማረኝ፣ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን፣ ልጄ ሆይ፣ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፣ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል፣ አንተም ትሣቀያለህ። ሉቃ. 16፥19-25

በዚህ ዓለም በኢኮኖሚ መበልጸግንና ምድራዊ ምቾትን በእግዚአብሔር ከመባረክና ከእምነት ትክክለኛነት ጋር የግድ ለማቆራኘትና የእነዚህ ውጤት መሆኑን ለማሳየት ብዙ የደከምከው ጸጋ አብ በቀለ እና መሰሎቹ ተሐድሶ ፕሮቴስታንቶች ሆይ፣ ታዲያ ይህን የጌታ ቃል እንዴት ታዩታላችሁ? ያ ባለ ጸጋ በምድር ላይ ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር እየለበሰ፣ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር የነበረው፣ በጌታ ቃል በተሐድሶ መንፈስ በመለወጡ ነበረን? እምነቱና ሕይወቱ ትክክለኛ ስለሆነ ነበረን? በአንጻሩ ደግሞ ድሀው አልዓዛር ያን ያህል በድህነት፣ በቁስል፣ በችጋር፣ እና በብቸኝነት በባለ ጸጋው ደጅ ወድቆ ቁስሉን ውሾች እስኪልሱት ድረስ በችግር መኖሩ በጌታ ቃል ባለመታደሱና እምነቱ ትክክል ባለመሆኑ የደረሰበት ነበረን? የምድሩን ብቻ ሳይሆን የሰማዩንም እናውቃለን የምትሉ



CamScanner

ተሐድሶ ፕሮቴስታንቶች ሆይ፣ እስኪ የዚህን ነገር ምክንያቱን አስረዱን!

5) "በጥናቱም የአሜሪካ የኢኮኖሚ ምጥቀት ምስጢር በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ላይ በመቆማቸው፣ ከሙስና የፀዱ በመሆናቸው፣ ለእርስ በርሳቸው ያላቸው ቤተሰባዊ ፍቅርና በወንጌል ሥነ ምግባር በታነጹ ክርስቲያን ባለ ራእይ አባቶች በመመራታቸው መሆኑን በዝርዝር አመለከተ" የሚለው ሀሳብ እስኪ ምን ያህል እውነት ነው? በእውነት የአሜሪካ ኢኮኖሚ ዕድገት "በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ላይ የቆመ" ነው? ከሙስና የጸዱ ናቸው? በወንጌል ሥነ ምግባር የታነጹ ናቸው? ከአፍሪካ የተወሰዱ ወገኖቻችን በባርነት የማቀቁት በማን ነበር? እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ የመምረጥና የመመረጥ መብት አጥተው፣ እንደ ዕቃ እየተሸጡና እየተለወጡ ላባቸውን ብቻ ሳይሆን ደማቸውን የተመጠጡት በማን ነበር ይሆን? አሁንስ ድረስ በየሰበብ አስባቡ አለምክንያት በከንቱ የሚገደሉት፣ ከዚህም የተነሣ "Black Lives Matter" የሚል እንቅስቀሴ እስከ መጀመር የተገደዱት በምን ምክንያት ይመስልሃል? በወንጌል ሥነ ምግባር የታነጹ ክርስቲያን አባቶች የምትሏቸው እነዚህ ናቸው?

ምናልባት የእናንተ ወንጌል ሰውን በቆዳው ቀለም ምክንያት ይህን የመሰለ ግፍ መፈጸምን ይደግፋል ይሆን? እንዲያው በእውነቱ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዴት እንደ መጣ አለማወቅና እንደዚህ ብሎ ደፍሮ መጻፍ ምን ያህል አላዋቂነትና ጭፍን የአእምሮ ባርነት ላይ መውደቅ መሆኑን ሳስበው ይህ ወንድሜና እርሱን መሰል ሌሎች ወገኖቼ በጣም ያሳዝኑኛል። እነዚያ ከአፍሪካ የተወሰዱትና "ባሪያዎች" የተደረጉት ያለ ፈቃዳቸው በኃይል ነበር፣ የዛሬዎቹ ደግሞ ራሳቸውን በፈቃዳቸው ባሪያዎች አድርገዋል።

6) ይህን ጥናት አደረገ የተባለው ዞሀ ቼአ የተባለው ሰው "ክርስቶስ ኢየሱስን ተቀብሎ የተጠመቀው"፣ ክርስትና ለኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚጠቅም ስለተረዳ ከሆነ፣ አንድ ሰው ክርስቶስ ኢየሱስን የሚቀበለውና የሚጠመቀው በዚህ መንገድ መሆን አለበት? ክርስትና ለኢኮኖሚ ዕድገት ጠቃሚ መሆኑን ባይረዳ ኖሮ ክርስቲያን ላይሆን ነበር ማለት ነው? የዚህ አንድምታው ምንድን ነው? ክርስቶስ ኢየሱስ ያስተማረን ክርስትና እንደዚህ ያለ ነው? ክርስቲያን የምንሆንበት ምክንያትስ ይህ ነው?

7) "የኋላ ቀርነታችን፣ የድህነታችን፣ የረሃብተኛነታችን፣ የስደተኛነታችን፣ የመንደርተኛነታችን መሠረትና ምንጩ በክርስትና ስም ድግምት አስማትና ጥንቆላ በማስፋፋታችን ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።" (ገጽ

41) - እዚህ ላይ "የሚሉ ብዙዎች ናቸው" ይላል እንጂ "ብዙዎች" ካላቸው መካከል አንድ እንኳ ማስረጃ አልጠቀሰም። እነ ማን ናቸው? አልተጠቀሱም! ቢጠቅስ ነገሩ ትክክል ይሆናል ማለት ባይሆንም ግን ይህን የመሰለ መደምደሚያ ላይ ሲደርስ እንዲሁ በደፈናው "ብዙዎች ናቸው" ከማለት ይልቅ ምስክር መጥቀስ ተገቢ ነበር። ብዙዎቹ፤ ሐሳቦች እንዲህ ያሉ ናቸው፤ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያላቸውን ግላዊና ግምታዊ ጥላቻ ሳይንሳዊና ጥናታዊ አስመስለው ለማቅረብ የሚሞክሩ አታላዮችና ሐሰተኞች ናቸው።

8) ኢትዮጵያ አገራችን አሁን ያለችበትን ሁኔታ በተሳሳተ መነጽር በመመልከትና በተሳሳተ መለኪያ በመለካት የተገለጸው ድምዳሜ እጅግ የተሳሳተ ነው። የተሳሳተ የነገረ ሃይማኖት እና የታሪክ አረዳድ ውጤት ነው። ኢትዮጵያ እንደ አገር የኖረችበትንና ያለፈችበትን የራሷን ታሪካዊ ሂደትና ጭብጥ የዘነጋና የኢትዮጵያን ታሪክና ኩነት በአውሮፓውያን የታሪክ አረዳድና አስተሳሰብ መነጽር ከማየትና ከመረዳት የተፈጠረ የከባድ ስህተት ውጤት ነው።

## 7.2 የክርስትና ግቡ እና መለኪያው ምንድን ነው?

የተሐድሶ ፕሮቴስታንት ሰባኪዎች በመጻሕፍቶቻቸው በተደጋጋሚ፤ የሃይማኖት ተሐድሶ ለኢኮኖሚ ብልጽግና መሠረት እንደሆነ እና የኢኮኖሚ ብልጽግናም የክርስትና ሃይማኖት ዋና ዓላማ እንደሆነ አድርገው ይጽፋሉ። በውኑ የክርስትና ዓላማው ምድራዊውና ቁሳዊው ብልጽግናና ዕድገት ነውን?

የክርስትና ሃይማኖት ዓላማው ምን ስለመሆኑ ራሱ ባለቤቱ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይታበል ቃሉ እንዲህ ሲል አስተምሮናል፡ - "ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ፣ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" ማር. 8፡36 ይህም ማለት የክርስትና ዋናው ዓላማ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንጂ "ዓለምን ማትረፍ" እና የምድራዊ ሕይወት ስኬት ጉዳይ አይደለም ማለት ነው። እርሱ "ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" ብሎናልና። ማቴ. 6፡33 እንዲሁም "በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም" ተብለናል። ቆላ. 3፡1-2

ስለሆነም የክርስቲያን ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን መንግሥቱንና ጽድቁን መፈለግ እንጂ ምድራዊ የሆነውን ብልጽግናና ቁሳዊ ሀብትን መሻት አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚህኞቹ እስከ ሠራን ድረስ ለሚያምኑት ብቻ ሳይሆን ለማያምኑትም እንኳ የሚሰጡ ተራ ነገሮች ናቸውና። በዚህ ዓለም ያሉ ነገሮች የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን የሚሰጡን የሃይማኖት ዋጋዎች ሳይሆኑ ለሚሠራ ሁሉ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው፣ ሰው በመሆናችን የሚሰጡ ናቸው። ጌታችን ይህን ሲያስረዳ "እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፣ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" እንዳለ። ማቴ. 5፡45 ኢየሱስ ክርስቶስ የክርስትና ሃይማኖትን የሰጠው ሰዎችን በዚህ ምድር ላይ ባለጸጎችና ቅምጥሎች ለማድረግ ሳይሆን "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" በማለት ለምድራዊ ተጋድሎ ለሰማያዊ ክብር ነው። ማቴ. 16፡24

እንደዚሁም መሠረታዊ በሆነው የወንጌል ትምህርቱ ላይ ጌታችን እንዲህ ብሎ አስተምሮናል፡-

> እርሱም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዓይኑን አንሥቶ እንዲህም አላቸው፡- እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና። እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፣ ትጠግባላችሁና። እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፣ ትስቃላችሁና። …ነገር ግን እናንተ ባለ ጠጎች ወዮላችሁ፣ መጽናናታችሁን ተቀብላችኋልና። እናንተ አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፣ ትራባላችሁና። እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ፣ ታዝናላችሁና ታለቅሱማላችሁ። ሉቃ. 6፡20-21 ፤ 24-25

እስኪ አንድ አፍታ ቆም ብለን እናስብ! በዚህ የጌታችን ትምህርት ውስጥ ቁሳዊ የኢኮኖሚ ብልጽግናና ዕድገት የክርስትና ዓላማና ተግባር ይህ ስለ መሆኑ የሚናገር ቃል የት አለ? ይልቁንስ ቅዱስ ቃሉ ከዚህ በተቃራኒ የሚናገር አይደለምን? "እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፤ ... እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፤ ... አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፤ ... ነገር ግን እናንተ ባለ ጠጎች ወዮላችሁ፤ ... እናንተ አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፤ ትራባላችሁና። እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ" የሚል አይደለምን? በዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሚያምን ሰው አንድን አገር በሀብቱ ብዛትና በኑሮው ምቾት መሠረት በእግዚአብሔር የተባረከ ነው ለማለት የሚችለው እንዴት ነው? እንደዚህ ያለው አስተሳሰብ የሚሠራው በኦሪቱ ነበር። በዘመነ ኦሪት ልጅነት ያልተሰጠበትና ሰማያዊ ጸጋ የተዘጋበት ዘመን ስለነበረ ሕጉን ለሚጠብቁ ሰዎች ተስፋ ተደርጎ የተሰጣቸው በምድር ላይ እድሜ መርዘምና የከረመውን እህል መብላት ነበር። በዘመነ ወንጌል ግን ይህ ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። በወንጌል ዘመንማ "እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ" ተባለ! በዘመነ ኦሪትም ቢሆን እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች የኖሩት በምቾት ሳይሆን በስደትና በመከራ ውስጥ ነበር።

ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ ሲናገር "ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፤ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም" ብሏል። ሉቃ. 9፡58 ጌታችን በተግባር ኖሮ ያሳየንና ያስተማረን በቅዱስ ቃሉም የነገረን እንደዚህ ነው። በዘመነ ወንጌል እግዚአብሔር እርሱን በእውነት ሊያገለግሉት የሚፈልጉ ሰዎችን "ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ" ይላል እንጂ ሀብት ንብረት አከማች፣ በቁሳዊ ሀብት በልጽግ አላለም። ማቴ. 19፡21 በብሉይ ኪዳን እንኳ በክህነት ያገለግሉት ዘንድ እግዚአብሔር መርጧቸው የነበሩት አሮንና መላው የሌዊ ነገድ ከሌላው ነገድ ተለይተው የመሬት ርስት አልነበራቸውም። በእግዚአብሔር መመረጥ ማለት በምድራዊ ሀብት መበልጸግ አይደለምና።

በምድራዊ ሀብትና ድሎት መኖር የፈርዖን አገልጋዮች ጠባይ ነው። በዮሴፍ ዘመን በግብጽ ምድር ተከስቶ ከነበረው ረሃብ የተነሣ "ዮሴፍም የግብፅን ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛ፤ የግብፅ ሰዎች ሁሉ ራብ ስለ ጸናባቸው ርስታቸውን ሸጠዋልና፤ ምድሪቱ ለፈርዖን ሆነች" ካለ በኋላ ቀጥሎ እንዲህ ይላል፡- "የካህናትን ምድር ብቻ አልገዛም፤ ካህናቱ ከፈርዖን ዘንድ ድርጎ ያገኙ ነበርና፤ ፈርዖንም የሰጣቸውን ድርጎ ይበሉ ነበር፤ ስለዚህም ምድራቸውን አልሸጡም።" ዘፍ. 47፡ 20፤ 22 የፈርዖን ካህናት የሚታረስ መሬት ነበራቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ ከፈርዖን ዘንድ ድርጎ (ቀለብ) ይቀበሉ ነበር። ስለሆነም ሌላው ሕዝብ ሲቸገር እነርሱ ግን ባለጸጎች ስለነበሩ አልተቸገሩም። ምድራዊ ባለጸግነት የፈርዖን አገልጋዮች ጠባይ እንጂ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ጠባይ ወይም መገለጫ አይደለም። የተሐድሶ



CamScanner

ፕሮቴስታንቶች ጥረት የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ወደ ፈርዖን አገልጋዮች ለመለወጥ ነው።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ወዳጆች በዚህ ዓለም እንዴት እንደ ኖሩና ምን እንዳገኙ ቅዱስ ጳውሎስ በግልጥ ነገሮናል፤ እንዲህ ብሎ፡-

> ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ፣ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፣. . . ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ። እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፣ . . . ዕብ. 11፥36-40

እስኪ እዚህ ላይ የተዘረዘሩትን በእግዚአብሔር እውነተኛ ወዳጆች ላይ የደረሱባቸውን ነገሮች አንድ ጊዜ መለስ ብለን አንድ በአንድ እያስታወስን ከልብ እናስባቸው።

የእግዚአብሔር አገልጋዮችማ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ገለጸው "በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጦም፣ . . . ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ፣ በክብርና በውርደት፣ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ" ራሳቸውን የሚያቀርቡ ናቸው። እንደዚሁም "ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው" በማለት ከዚህ ዓለም ሀብትና ብልጽግና ባዶዎች የሆኑ ድሆችና ችግረኞች፣ ሆኖም ግን በመንፈሳዊው ሀብት የበለጸጉና ሌሎችንም የሚያበለጽጉ ሀብታሞች ናቸው። 2 ቆሮ. 6፥5-10

ይኸው ሐዋርያ በአንደኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ፣

> ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፣ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር፣ የተናቀውንም ነገር፣ ያልሆነውንም ነገር መረጠ።

በማለት ይህንኑ እውነታ በአጽንኦት ገልጾታል። 1 ቆሮ. 1፥26-28

እንደዚሁም የእግዚአብሔር ቃል "የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ፣ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?" በማለት የተሐድሶ ፕሮቴስታንቶችን ሐሳብ በግልጽ ይቃወማቸዋል። ያዕ. 2፥5 የጌታን መወለድ መጀመሪያ ለማየት የታደሉትና ከቅዱሳት መላእክት ጋር

ለመዘመር የተጠሩት እረኞች ነበሩ። ከእርሱ ጋር እንዲኖሩና በኋላም የምሥራቹን ቃል ወንጌል ለዓለም እንዲሰብኩ የመረጣቸው ሐዋርያት ድሆች ነበሩ። ጌታችንም በዚህ ዓለም ላይ ሲኖር የመረጠው ድህነትን ነበር፤ ስለዚህም ነው ሲወለድ በከብቶች በረት፣ ሲያስተምር የሰው ጀልባ ለምኖ (የጴጥሮስን)፣ ራሱን የሚያስጠጋበት ያልነበረው፣ ፋሲካን ሲያከብር በሌላ ሰው ቤት፣ ሲቀበር በሌላ ሰው መቃብር ነበር። የሁሉ ጌታ ሲሆን ስለ እኛ ሲል ድህነትን መረጠ፤ በዚህም የክርስትናን ሕይወት ምንነት በተግባራዊ አኗኗሩም አሳየን።

የክርስትና ሃይማኖት ዓላማ ምድራዊ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናና ሀብት ማስገኘት ነው ማለት ሃይማኖትን እንደ ፖለቲካ አስተሳሰብ ለምድራዊ ጥቅም ብቻ የሚያገለግል ባሪያ ለማድረግ መሞከር ነው። የክርስትና ሃይማኖት ግን ጊዜያዊና ኃላፊ ከሆነው ከዚህ ዓለም እጅግ የበለጠ የሆነ ሌላ አጀንዳ አለው። ስለዚህ የክርስትና ሃይማኖት የምድራዊ ነገሮች ማሟያና ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሳይሆን እነዚህን ነገሮች ሰው በመንገድ ላይ ሲጓዝ በጉዞው ላይ የሚገጥሙትን ነገሮች በሚመለከትበት ሁኔታ የሚመለከታቸው ተራ ነገሮች ናቸው። ክርስትና ለቁሳዊና ኢኮኖሚያዊ ነገሮች ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆኖ ያገልግል ማለት ከዋናው ምንነቱ አውጥቶ ሰው ሠራሽ የሆነ ሌላ ምንነትን በላዩ ላይ ለመጫን መሞከር ነው።

ይህ የተሐድሶዎች አስተሳሰብ ጌታችን በፈቃዱ በገዳመ ቆሮንቶስ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ከተቀበላቸው ፈተናዎች አንዱ የሆነውና "የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፣ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው" ተብሎ የተጻፈው ፈተና ነው። ታዲያ ጌታችን ምን አለው? መድኃኒታችን ዲያብሎስን "ያን ጊዜ ኢየሱስ፣ ሂድ፣ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና" ብሎ እንደ ውሻ አባረረው። ማቴ. 4፡8-10 ተሐድሶ ፕሮቴስታንቶችም እንደ አባታቸው ዲያብሎስ ከእግዚአብሔር ጋር መኖራችንን፣ የእርሱ ልጆች መሆናችንን፣ "የዓለምን መንግሥት የምታገኙበትን ሥራ ሥሩበት፣ ለምድራዊ ዓላማ አውሉት" ሲሉን፣ እኛም በጌታችን ቃል "ሂድ፣ አንተ ሰይጣን" ልንላቸው ይገባል። ይህ ዓይነቱ የተሐድሶ ፕሮቴስታንቶች አስተሳሰብ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለው የማያምኑ የነበሩ ቢሆኑም፣ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ለነበረው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ባለቤቶችና ጠባቂዎች ሆነው ወደ ቤተ መቅደሱ ይመጣ የነበረውን አሥራቱን በኩራቱንና የመሳሰለውን ገንዘብ እየተጠቀሙ በሀብት ከብረው እንደ ነበሩት እንደ ሰዱቃውያን መሆን ነው። ተሐድሶ ፕሮቴስታንቶች የዘመናችን ሰዱቃውያን ቢባሉ የሚበዛባቸው አይሆንም።

ስለሆነም የክርስትና ሃይማኖት መሠረታዊ ግቡ አንድን አገርና ሕዝብ በኢኮኖሚው ማበልጸግ በሥልጣኔው ማስመንደግ አይደለም። ይህ በእራት ላይ ዳረጎት እንደሚባለው ዓይነት የሆነ ነገር ነው። በዚያውም ላይ ለሚሠራ ለማንኛውም ሰው የሚሰጥ ነገር ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከታች እንደምናየው ከክርስትና ውጭ የሆኑም ሆነ የተለያየ እምነት ያላቸው ሕዝቦችና አገሮች በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ብዙ ተራምደዋል፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይም ደርሰዋል። ምክንያቱም ይህ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ትክክል በመሆን አለመሆኑ መሠረትነት አይደለምና። ስለሆነም የአንድ አገር የሚከተለው ሃይማኖት ትክክለኛ ስለመሆን አለመሆኑ መለኪያው የዚያ አገር አገራዊ የምርት መጠን ወይም የነፍስ ወከፍ ገቢ አይደለም። ይህ የተሐድሶች እጅግ የተሳሳተ እሳቤ ብቻ ነው።

ይህ ዓይነቱ ከክርስትና መሠረታዊ ዓላማና ትምህርት ተቃራኒ የሆነው የፕሮቴስታንቶች እሳቤና እምነት መሠረቱ ምንድን ነው? ከተባለ፣ የፕሮቴስታንቲዝም መሠረታዊ ባሕርይ ውጤት የሆነው "የብልጽግና ወንጌል" የሚሉት አስተምህሮና እምነት ነው።

**"የብልጽግና ወንጌል** - Prosperity gospel"

"የብልጽግና ወንጌል" - የሚለው አስተምህሮና እምነት በፕሮቴስታንቶች ውስጥ ባሉ የተለያዩ ግለሰቦችና አንጃዎች የሚታመን እምነት ሲሆን፣ ዋና አስተምህሮውም የእግዚአብሔር ዋናው ፈቃዱ በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ሀብታሞችና ጤናማዎች እንዲሆኑ ነው የሚል ነው።[49] "የብልጽግና ወንጌል" አማኞችና አስተማሪዎች፣ ሰዎች በእርሱ ካመኑ እግዚአብሔር ደግሞ ሀብትንና ጤናን አብዝቶ ይሰጣቸዋል፣ ቤተሰባዊ ሕይወታቸው ተድላ ደስታ የመላበት፣ ሥራቸው ሁሉ የተቃናና አሊጋ በአሊጋ ይሆናል ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በእግዚአብሔርና በአማኙ መካከል ላለው ለዚህ ስምምነት የውል ማረጋገጫ ነው ይላሉ።[50] የክርስቶስ አዳኝነት ከሕመምና ከድህነትም ጭምር ነው ያዳነን ይላሉ። በገንዘብ ባለ ጸጋ መሆን በእግዚአብሔር የመባረክ መገለጫና ውጤት ሲሆን፣ ድህነትና ደዌ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው በእግዚአብሔር ያለመባረክና የኃጢአተኛነት መገለጫዎችና ውጤቶች ናቸው ብለው ያምናሉ፣ ያስተምራሉ።[51]

በአጠቃላይ "የብልጽግና ወንጌል" መምህራን ድህነትን ከኃጢአትና ከኃጢአተኛነት ጋር ሲያያዙት፣ ኢኮኖሚያዊ ስኬትና ብልጽግናን ደግሞ በእግዚአብሔር ከመባረክና

[49] J. Matthew Wilson, *From Pews to Polling Places: Faith and Politics in the American Religious Mosaic.*

[50] Jonathan L.Walton, *Watch This! The Ethics and Aesthetics of Black Televangelism.*

[51] J. Matthew Wilson, *From Pews to Polling Places: Faith and Politics in the American Religious Mosaic.*



CamScanner

ከመቀደስ ጋር ያቆራኙታል።[52] የሀብት መብዛትና የሕይወት መመቸት የእውነተኛ እማኝ መገለጫዎች ናቸው፣ ድህነት ደግሞ የእምነት ማጣት ውጤት ነው ይላል። ለዚህም የሚጠቅሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሏቸው፣ ሆኖም ጥቅሶቹን ለዚህ እምነታቸው እንዲስማሙ አድርገው ከዐውዳቸው ውጭ ይጠቅሷቸዋል ይተረጉሟቸዋል።[53]

ይህ አስተሳሰብና እንቅስቃሴ ብቅ ያለው በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ በ1950ዎቹ ላይ ነበር፣ አንዳንዶች ግን ወደ 19ኛው መቶ ዓመት ይስቡታል። ከዚያም በ1980ዎቹ በአሜሪካ እንደ ፋሽን ተይዞ በነበረው ቴሌኤቫንጀሊዝም ሥር እየሰደደ መጣ። በ1990ዎቹ እና በ2000ዎቹ ላይ በጴንጤ ቆስጤዎች እና በሌሎችም የፕሮቴስታንት ቡድኖች አማኞችና መሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ እሳቤና አስተምህሮ ሆኗል። ከዚያም ወደ ሌላው ዓለም ተሰራጭቷል።[54] ይህ አስተምህሮና እምነት የተፈጠረውና ተቀባይነት ያገኘው በፕሮቴስታንቶች ውስጥ በተለይም በጴንጤ ቆስጤ ቸርቾች ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም መንፈሳዊ ጸጋን እሁኑኑ እና ወዲያውኑ በቶሎ ማግኘት ላይ፣ ፈውስንም ቶሎ ማግኘትና መስጠት ላይ ያተኩሩ ስለሆኑ ነው። በ2006 (እ. ጎ. አ) በታይም መጽሔት በተደረገ ጥናት መሠረት በአሜሪካ ክርስቲያኖች ነን ከሚሉት ውስጥ 17% ያህሉ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ነን ብለዋል።[55]

የዚህ እምነት ተከታዮች፣ በ2000ዎቹ የቅርብ ዓመታት ውስጥ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች የብልጽግና ወንጌልን ተቀብለዋል ይላሉ።[56] በእነዚህ የቅርብ ዓመታት ውስጥ ይህን እምነት የሚያስተምሩ ቸርቾች በፍጥነት እየተስፋፉ የመጡት በሦስተኛው ዓለም አገራት ነው።[57] በዚህ ላይ ጥናት ያደረገው ፊሊፕ ጀንኪንስ የተባለው ሰው "በድሀ አገሮች የሚገኙ ድሀ ዜጎች ከድህነታቸው የሚያወጣቸው ስለሚመስላቸውና አስተምህሮው በተአምራት ላይ ከፍ ያለ አጽንኦት ስለሚሰጥ ይህን አስተምህሮ ሳቢና ማራኪ ሆኖ ያገኙታል" ይላል።[58] ይህ እምነት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ካሉባቸው አካባቢዎች አንዱ ምዕራብ አፍሪካ ሲሆን በተለይም ናይጀሪያ ይህ እምነትና መንፈስ በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋባት አገር ናት።[59] ከፕሮቴስታንቶች መካከል ይህን አስተምህሮ ሐላፊነት የጎደለው ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣

[52] Kate Bowler, *Blessed: A History of the American Prosperity Gospel.*

[53] Philip Jenkins, *The new Faces of Christianity: Believing the Bible in the Global South..*

[54] Jonathan L.Walton, *Watch This! The Ethics and Aesthetics of Black Televangelism.*

[55] Jeff Chu, van Biema, David, *Does God Want You To Be Rich?, Time.*

[56] *Hanna Rosin, "Did Christianity Cause the Crash?.*

[57] Jenkins, Philip, *The Next Christendom: The Coming of Global Christianity.*

[58] እንደ ላይኛው

[59] እንደ ላይኛው



CamScanner

ጣዖት አምልኮን ያስፋፋል በማለት አጽንተው የሚቃወሙትም አሉ።

"የብልጽግና ወንጌል" አማኞችና አስተማሪዎች፣ እኛ ያደረግነው ጠፍቶና ተዘንግቶ የነበረውን እውነተኛውን የክርስትና አስተምህሮ ዳግመኛ መመለስ ነው እንጂ አዲስ ነገር አላመጣንም ይላሉ። እንዲሁም ሴኪዩላር በሆነው ኅብረተሰብ ላይ ክርስትና የበላይነት እንዲኖረው ለሚደረገው እንቅስቃሴ አንደኛው መንገድ ነው ይላሉ።[60] በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል ተስፋ ተደርጎ የተሰጠው ምድራዊ በረከትና ድል አድራጊነት ዛሬ ላሉ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖችም ይሠራል ሲሉ ለመሞገት ይሞክራሉ።[61] ምጽዋትን መስጠት ደግሞ ከእግዚአብሔር ሀብትን ለማግኘት እንደ ዋና መሣሪያ ነው ይላሉ። ብዙ የፕሮቴስታንት አማኞች ለቸርቾቻቸውና ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ገንዘብ የሚሰጡትና ምጽዋትም የሚመጸውቱት ከእግዚአብሔር የበለጠ ሀብት ለማግኘት ነው ይላሉ።[62] ምጽዋትንና መስጠትን የሚቆጥሩት እንደ ኢንቨስትመንት ነው።

ይህ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት፣ መከራ ስለ መቀበል፣ ስለ ፍርድ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎችንና ጥቅሶችን አይወዳቸውም። ስለዚህ እንደ ሌሉ ያህል ያልፉቸዋል።

አሜሪካዊ ለሆነው ለብልጽግና ወንጌል አስተሳሰብ መፈጠርና ማደግ አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላው ነገር ደግሞ ማክስ ዌበር ያዳበረው "ፕሮቴስታንታዊ የሥራ ባህል" የሚለው አስተሳሰብ ነው። ይህ ጉዳይ ከታች በ7.4 ላይ ተዳስሷል። የዚህ አስተምህሮ ሰባኪ የነበረው ሩሴል ኮንዌል የተባለ ፓስተር በ1915 ላይ በጣም ችግረኞችና ድሆች ለነበሩት ተሰባኪዎቹ "ሀብታም ልትሆኑ ይገባችኋል ብያችኋለሁ፤ ድሀ የመሆን መብት የላችሁም" ብሏቸዋል።[63] በ1936 ላይ ደግሞ ቻርለስ ፊልሞር የተባለ የዚሁ "የብልጽና ወንጌል" እምነት ዋና ደጋፊና አስተማሪ መዝሙር 23ን ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ እንደ ቀረበው አድርጎ እንደ አዲስ ጽፎታል።[64]

| | የመጽሐፍ ቅዱሱ ቃል | የብልጽግና ወንጌል ትርጉም ቃል |
|---|---|---|
| ፩ | እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣ የሚያሳጣኝም የለም። | The Lord is my banker; my credit is good.<br>እግዚአብሔር የእኔ ባንከር ነው፣ የሂሳብ መጠኔም ጥሩ ነው። |
| ፪ | በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። | He maketh me to lie down in the consciousness of omnipresent abundance;<br>በሁሉም ቦታ ምሉዕ የሆነውን መትረፍረፍ አውቄ እንድተኛ ያደርገኛል። |
| ፫ | ነፍሴን መለሳት፣ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። | He restoreth my faith in His riches;<br>He guideth me in the paths of prosperity for His name's sake.<br>በእርሱ ባለ ጸጋነት ያለኝን እምነት መለሰልኝ፤ ስለ ስሙም በብልጽግና መንገድ መራኝ። |
| ፬ | በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ<br>አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤<br>በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል። | He giveth me the key to His strongbox.<br>Yea, though I walk in the very shadow of debt, I shall fear no evil, for Thou art with me;<br>Thy silver and Thy gold, they secure me.<br>የካዝናውን ቁልፍ ሰጠኝ። በብድር ሸለቆ ውስጥ እንኳ ብሄድ፣ ክፉን አልፈራም፣ አንተ ከእኔ ጋር ነህና፤<br>ብርህ እና ወርቅህ እነርሱ ይጠብቁኛል። |
| ፭ | በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፣ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፣<br>ጽዋዬም የተረፈ ነው። | Thou preparest a way for me in the presence of the collector;<br>Thou fillest my wallet with plenty; my measure runneth over.<br>ገንዘብን በሚቀበለውና በሚሰበስበው ሰው ፊት መንገድን አዘጋጀህልኝ፤<br>ከረጢቴን በገንዘብ ሞላህ፤ መጠኑም የተትረፈረፈ ነው። |

| | | |
|---|---|---|
| ፮ | ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፣ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ። | Surely goodness and plenty will follow me all the days of my life,<br>And I shall do business in the name of the Lord forever.<br><br>ደግነትህና መትረፍረፍህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፣<br><br>በእግዚአብሔርም ስም ሁል ጊዜ ቢዝነስ አደርጋለሁ። |

ከላይ የተመለከትናቸውና ፕሮቴስታንቱ ጸጋ አብ በቀለ ያንጸባረቃቸው ሐሳቦችና አቋሞች የዚህ "የብልጽግና ወንጌል" አስተምህሮ ውጤቶችና መገለጫዎች ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ራሱ የዚሁ ኢክርስቲያናዊ የሆነው አስተምህሮ ተጠቂ ሆኖ ሳለ መልሶ በእኛ አገር እንደ እንጉዳይ ብቅ ብቅ ባሉ የፕሮቴስታንት ቸርቾችና ፓስተሮች ዘንድ ይህ ሁኔታ ተስፋፍቶ ማየቱን በማዘን መግለጹ ነው። በምሬት ሆኖ በመጽሐፉ ላይ ከገለጸው የሚከተለውን እንመልከት፡-

- "ገንዘብ ለወንጌል አገልግሎት አስፈላጊ እንደሆነ፣ ለወንጌል አገልግሎት ቅዱሳን ገንዘባቸውን እንዲሰጡ ማስተማር እንደሚገባ ባምንም በተቃራኒው ገንዘብ ተኮር ኮንፈረንሶች የወንጌል መድረኮች እንደሆኑ አላምንም። ዘማሪ ለገሠ ጂሎ "ሲዳማ አካባቢ የሚገኙ ነቢያትና የስህተት አሠራር በሕዝቡ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት እያስተከተለ ያለውን ቀውስ" (2006 ዓ. ም.) በሚል ርእስ ባዘጋጀው አስደንጋጭ ጥናት፣ በአዋሳ፣ በአለታ ወንዶ፣ በባንሳ ዳዬ፣ በወጂግራ፣ በወንዶ ገነት፣ በዳራ ወረዳዎች፣ በሐሰተኛ ነቢያት ገሃድ የወጣ ርኩሰት፣ ምዝበራ፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አካሄድና ልምምዶች ቤተ ክርስቲያን በአደጋ ላይ መሆኗን ሰሚ ካለ ይጮሃል። በአንድ ኮንፈረንስ ስለ ተደረገው የገንዘብ ማስለቀቂያ ሁኔታ እንዲህ ብለዋል፡-
  - "አገልጋዩ" ባለ 100 ብር ዘርዝሮ እያንዳንዱ ብር ዘይት ተቀብቶ ተጸልዮበታል፤ በማለት የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን ብር በ1,000 ብር የሚገዛ ንግዱ ይባረካል፣ ሰዎች በጥንቆላና በአስማት ገንዘብ እየሳቡ ያገኙ የለም ወይ? እኛም በኢየሱስ ስም በተጸለየ ብር ገንዘብ እንስባለን፣ በሳጥናችሁ ውስጥ አስቀምጡት፣ ይህን ብር ምንም ቢቸግራችሁም አታውጡት በማለት በቅርቡ በአንድ ኮንፈረንስ ላይ 99,000 ብር ሰብስቧል ብሏል።" (ገጽ 295)

፩ "ከእግዚአብሔር ቃል የተፋታ መንፈሳዊ ልምድ መንሰራፋት። በገጠርም ሆነ በከተማዎች ያለው ምስኪንና የዋህ ሕዝብ በእግዚአብሔር ተናገረኝ ስም እየተመዘበረ ነው። ለምሳሌ፡- "ይህን ጧፍ ወይም ሻማ በቤቱ ያበራ ታላቅና ድንቅ ተአምራት በቤቱ ይሆናል" ብለው አንድ ጧፍና ሻማ ከ1,000 እስከ 2,000 ብር በሰልፍ ሕዝብ በኮንፈረንስ ሜዳ እንዲገዙ ሲያደርጉ አጠገቡ የነበረ ወንድም ልቡ ተሰብሮ ያጫወተኝ ትዝ ይለኛል። ከኬንያ ከቀደምት የፔንቴኮስታል ሰባኪዎች አንዱና በዓለም ላይ በአገልግሎቱ አዎንታዊ ተጽእኖው የተገለጠው ቢሾፕ ዶ/ር ጆካዩ በመጽሐፋቸው "በደቡብ አፍሪካ አንዳንድ ሰባኪዎች ልዩ ኃይል በአገልግሎታቸው እንዲገለጥ ደጋሚዎች ቤት መሄድ እንደ ጀመሩና በመድረኮቻቸው አንዳንድ የተደገመበትን ዕቃ ማስቀመጥ እንደ ጀመሩ" ይናገራሉ።" (ገጽ 296)

ምንም እንኳ እንዲህ ቢልም፣ የራሱ የጸጋ አብ በቀለ ከላይ ያየናቸው ክርስትናን ከቁሳዊ ብልጽግና ጋር የሚያስተሳስሩት ሐሳቦቹ የዚሁ የብልጽግና ወንጌል አስተምህሮና እምነት ውጤቶች ናቸው። የምናምነው እምነት ትክክል ቢሆን ኖሮ፣ የምንሰብከው ወንጌል እውነተኛውን ወንጌል ቢሆን ኖሮ አገራዊ የምርት መጠናችን ያደገ የነፍስ ወከፍ ገቢያችን የበዛ ቁሳዊ ሀብት የሞላልን ባለጸጎች እንሆን ነበር የሚለው ሐሳቡና እምነቱ የብልጽግና ወንጌል ራሱ ነውና።

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገንዘብ እና ስለ ቁሳዊ ብልጽግና ምን ይላል?

መድኃኒታችን ገንዘብን በተመለከተ "ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ . . . ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም" ብሏል። ማቴ. 6፡24 ይህን የጌታን ትምህርት የሰሙ ገንዘብን የሚወዱ ፈሪሳውያን ምን እንዳደረጉ ቅዱስ ወንጌል ከዚያው ቀጥሎ እንዲህ ይለናል፡- "ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር።" ሉቃ. 16፡14 ገንዘብን መውደዳቸው በጌታችን ትምህርት ላይ እንዲያፌዙ አደረጋቸው። እንደዚሁም "በገንዘብ ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው!" ብሏል። ማር. 10፡23-24 እንግዲህ ይህ ሁሉ የአምላክነት ቃሉ የሚነግረን ገንዘብ በራሱ ክፉ ባይሆንም ለሚወዱትና አጠቃቀሙን ለማያውቁበት ሰዎች ግን ከእግዚአብሔር ጋር ተነጻጻሪ እስኪሆንባቸው ሊደርስ የሚችል ጣዖት መሆኑን ነው።

ቅዱስ ጳውሎስም "...አእምሯቸውም በጠፋባቸው፣ እውነትንም በተቀሙ፣ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን የሚመስላቸው ሰዎች" በማለት እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ለቁሳዊ ነገር ማግኛ (ማትረፊያ) ሲሉ የሆኑ ሰዎችን "አእምሯቸው የጠፋባቸው" እና "እውነትን

የተቀሙ" ሲል ገልጿቸዋል። የክርስትናን ዓላማና ግብ በገንዘብ መክበርና በቁሳዊ ነገሮች መበልጸግ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች፣ በቅዱስ ጳውሎስ አገላለጽ "አእምሯቸው የጠፋባቸው" እና "እውነትን የተቀሙ" መባላቸውን ልብ ማለት ይገባል። 1 ጢሞ. 6፥5

ቅዱስ ጳውሎስ በመቀጠልም እንዲህ ይላል፡-

> እንደነዚህ ካሉት ራቅ። . . . ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያስንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፣ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፣ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ። 1 ጢ.ሞ. 6፥9-11

ኃጢአት የሚሆነው ገንዘብ ያለው መሆን ወይም ሠርቶ ማግኘት አይደለም። ክርስቲያኖች ጠንክረው ሊሠሩና ራሳቸውን ሊችሉ እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን በተመለከተ እንዲህ ሲል በአጽንዖት አስተምሯልና፡-

> ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፣ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፣ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፣ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም። ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን፣ **ሊሠራ የማይወድ አይብላ** ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፣ በሰው ነገር እየገቡ፣ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ። 2 ተሰ. 3፥8-13

ስለሆነም ተግቶ መሥራት፣ መልካም ሥራን ለመሥራት አለመታከት፣ ራስን መቻልና ለሌላውም መትረፍ ክርስቲያናዊ ተግባራትና ግዴታዎችም ናቸው። ሆኖም ግን ሠርቶ ገንዘብ ማግኘትና በገንዘቡ መጠቀም እና ገንዘብን መውደድ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ገንዘብን በራሱ እንደ ግብ አድርጎ መመኘት በቅዱስ መጽሐፍ የተጠላ ነው። ክርስቲያኖች ከሚባሉ መካከል እንደዚህ ያለ ወንድም ቢኖር ቅዱስ ጳውሎስ "አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም **ገንዘብን የሚመኝ** ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፤ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ" ይላል። 1 ቆሮ. 5፥11

እንዲሁም "ወይም ሌቦች ወይም **ገንዘብን የሚመኙ** ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም" ይላል። 1 ቆሮ. 6፥10 በ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክት ላይም "ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ" ብሎ ያን ዘመን የሚያስጨንቅ እንደሚያደርጉት ከዘረዘራቸው ክፉ ምግባሮች መካል አንዱ ይኸው



CamScanner

ገንዘብን መውደድ ነው። "ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ . . . ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ" ይላል። 2 ጢሞ. 3፡1-4

ገንዘብን መመኘት ኑፋቄንና መናፍቃንን እንዲፈለፈሉ ምቹ መሬት ሆኖ የሚያገለግል ስለመሆኑም ቅዱስ ጴጥሮስ "ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፣ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ከደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፤ . . . ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል" ብሏል። 2 ጴጥ. 2፡1-3

ወደ ሐዋርያት የአንድነት ማኅበር ይገቡ የነበሩ ሰዎችን በተመለከተ "መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፣ በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር" ተብሎ ተጽፏል። የሐዋ. 4፡34-35 ገንዘቡን ያስቀምጡ የነበረው በሐዋርያት እግር አጠገብ ነበር፤ ምክንያቱም ገንዘብ አገልጋይ ስለሆነ ከእግር አጠገብ ሊቀመጥ እንጂ ከጎን አብሮ እኩል ሊቀመጥ አይገባውምና። ገንዘብ እንደ አገልጋይነቱ ሊሆን ከሚገባው ከእግር ሥር መሆኑ ቀርቶ ከጎን አብሮ እኩል ካስቀመጡት፣ ከዚያም አልፎ ራስ ላይ ካወጡት፣ ያን ጊዜ ከእግዚአብሔር አምላክነት ጋር የሚገዳደር ጠላት ይሆናል። ስለዚህም ገንዘብን በአግባቡ መጠቀም እንጂ ራሱን መውደድ አደገኛ ስለሆነ "አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን" ተብለናል። ዕብ. 13፡5

ስለዚህ አሁንም በድጋሚ ለማስታወስ ገንዘብ በራሱ ኃጢአት አይደለም፣ ባለ ጸጋ መሆንም ኃጢአት አይደለም። ክርስቲያኖች ሊሠሩና ከራሳቸው አልፎ ሌሎችንም ሊረዱ ግዴታ አለባቸው። በየተሰማሩበት ሥራ ሁሉ ውጤታማ ሥራ በመሥራት ሥራን የመቀደስና መልካም አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። ታላላቅ የእግዚአብሔር ወዳጆች የነበሩት እነ አብርሃም፣ እነ ኢዮብ፣ ዳዊት፣ . . . ባለ ጸጋዎች ነበሩ። ሆኖም በመንፈስ ግን ድሆች ነበሩ፣ ማለትም ሀብቱ የእግዚአብሔር እንጂ የራሳችን ነው ሳይሉ የኖሩ ነበሩ እንጂ በሀብታቸው ያልተመኩ፣ ራሳቸውን እንደ ባለ ጸጋ የማይቆጥሩ ነበሩ። ባለ ጸጋ መሆን ኃጢአት እንዳልሆነው ሁሉ በስንፍና ምክንያት ድሀ መሆንም ጽድቅ አይደለም። ዋናው የሕሊና ወይም የአስተሳሰብ ጉዳይ ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ባለ ጸጋ ቢሆንም በመንፈስ ድሀ ነው፣ ምንም ሳይዝ ወደ ዓለም እንደ መጣና ባዶውን ወደ መቃብር እንደሚወርድ ያውቀዋልና።

በአንጻሩ በተለያየ ምክንያት ድሀ ቢሆንም የባለ ጸጋነት ምኞት በውስጡ ካለበት ደግሞ ይህ ጉስቁልና ነው። ንጉሡን አክአብንና ንግሥቲቱን ኤልዛቤልን የድሀውን የናቡቴን የወይን ቦታ ለመንጠቅ ሲሉ በግፍ ያስገደሉት ድሆች ሆነው ችግሯቸው



CamScanner

አልነበረም፣ የባለ ጸጋነት ምኞት አንዴ አእምሮን ከተቆጣጠረ ማቆሚያ ስለሌለው ነው እንጂ። ይሁዳ ባለ ጸጋ አልነበረም፣ ድሀ ነበር እንጂ። ሆኖም ግን በውስጡ የነበረው የገንዘብ ፍቅር ጌታውን እስከ መሸጥ አድርሶታል።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚቃወመው ሀብትን ሳይሆን ገንዘብን መውደድን ነው፤ ምክንያቱም ሐዋርያው እንደ ገለጸው "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና።" የገንዘብ ፍቅር - መዋሸትን፣ መማልን፣ ማጭበርበርን፣ ማታለልን፣ የሌላውን መመኘትን፣ ራስን ለሰይጣን ተገዥነት አሳልፎ መስጠትንና ገባሪ መሆንን፣ ሌሎችን መውረርን፣ ጦርነትን፣ መግደልንና ይህን የመሰለውን ወንጀል ሁሉ ወደ መፈጸም የሚወስድ ክፉ ደዌ ነውና። ከብዙ ወንጀሎች ጀርባ ገንዘብ አለ የሚባለው ለዚህ ነው። መሥራትና ገንዘብ ማግኘት፣ ገንዘብን እንደ አገልጋይነቱ መጠቀም ተገቢ ነው፤ ጌታ ማድረግና በፍቅሩ መነደፍ ግን ገዳይ ነው።

CamScanner